# ለሂደት መዘጋጀት

Inova Loudoun Hospital

## እንኳን ደህና መጡ

በቀጣይ ለሚያደርጉት ሂደት Inova Loudoun Hospital ስለመረጡ እናመሰግናለን። ደህንነቱ በተጠበቀ ከፍተኛ ጥራት ያለው እንክብካቤ ለማቅረብ እንሰራለን። በ Inova Loudoun Hospital በፍቅርና እንክብካቤ እናገለግሎታለን።

ይህ መመርያ ለሂደትዎ በምን መልክኩ እንደሚዘጋጁ፣ ወደ ሆስፒታሉ ከመጡ በኋላ ምን እንደሚጠበቁና ከቀዶ ጥገና በኋላ እንክብካቤዎን በምን መልኩ እንደሚያቅዱ የሚሉትን መረጃዎች የሚያካትት ነው። ተጨማሪ ጥያቄ ካሉት እባክዎትን ቀዶ ጥገና ለሚያካሂደው ወይ ከሂደትዎ በፊት ቃለ መጠይቅ ላደረገሎት የህክምና ቡድን ያናግሩ።

### የመጀመርያ ሂደት

ለሂደቱ ቀጠሮ ካስያዙ በኋላ ከቀዶ ጥገና በፊት ለሚደረገው ቃለ መጠይቅ ቀጠሮ ለመያዝ ከ Inova Pre-Procedural Evaluation Clinic ይደወልሎታል።

- አብዛኛው ግዜ ከቀዶ ጥገና በፊት የሚደረገው ቃለ መጠይቅ በአካል ወይ በስልክ የሚካሄድ ሲሆን ከ 30 እስከ 90 ደቂቃ ሊወስድ ይችላል።
- እባክዎትን ቀጠሮ በምንይዝበት ግዜ አስተርጓሚ ካስፈለግዎት ያሳውቁን።

ቃለ መጠየቅ ወይ በሚጎበኙበት ግዜ የህክምና ቡድን አባላት የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡

- የሜዲካል ታሪክና መድሃኒት ግምገማ
- ከቀዶ ጥገና በፊት የሚያስፈልጎትን ማንኛውም ምርመራ መለየት
- ለሂደትዎና ማደንዘዣ ዝግጁ እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑትን መመርያዎች መስጠት
- ጥያቄዎኞን መመለስ

ለዳሌ ወይ ጉልበት ቀዶ ጥገና ቀጠሮ ከያዙ በመገጣጠምያ ካምፓችን በታ ለማስያዝ እባክዎትን ወደ **703.858.6768** ወይ **703.858.8025** ይደውሉ።

INOVA®

## የቅድመ-ህክምና ግምገማ ክሊኒክ ዝግጅት

**የቅድመ-ህክምና ግምገማ ክሊኒክ የቀጠሮ ቀን፡**

---

**የቅድመ-ህክምና ግምገማ ክሊኒክ የቀጠሮ ሰዓት፡**

---

**Inova Pre-Procedural Evaluation Clinic**
Inova Loudoun Hospital
First Floor, North Tower
44045 Riverside Pkwy.
Leesburg, VA 20176
**P: 703.858.6768**

*እባክዎትን ወደ ሆስፒታሉ ተመላላሽ ታካሚዎች ላብራቶሪ ይግቡ።*

## ቃለ መጠይቅ ከማካሄዶ ወይ ወደ ክሊኒክ ከመግባቶ በፊት

**በሚከተለው መንገድ ለቃለ መጠይቅ ይዘጋጁ፡**

- ከሂደት በፊት የቀጠሮ ዎርክሽት ይሙሉ። እባክዎትን ቀጠሮ ለተያዘበት ቀን ወይ ቅድመ ቀዶ ጥገና ሲመጡ ይዘውት ይምጡ።
- MyChart ማግኘት ከቻሉ እባክዎትን የህክምና ታሪኮን ኦንላይን ይሙሉ። ወደ ሒሳቦ ለመግባት እባክዎትን **inova.org/mychart** ይጎብኙ።

## የቅድመ-ህክምና ግምገማ ክሊኒክ የቀጠሮ ወረቀት

**ከፋርማሲ የገዙት፣ የታዘዘሎት መድሃኒት፣ ቫይታሚን ወይ ኤሌክትሮሊት ጨምሮ አሁን የሚወስዷቸው መድሃኒቶች፡**

| የመድሀኒት ስም | የሚወስዱት መጠን | የቀጠሮ ሰዓት |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

**ከዚህ ቀደም የተካሄዱ ማደንዘዣ የሚፈልጉ ሂደቶችና ቀዶ ጥገናዎች፡**

---

---

---

---

---

**የመጀመርያ ደረጃ ሀኪምና ሌሎች ስፔሻሊስቶች ስም፡**

| የሀኪም ስም | ስፔሻሊቲ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## ሂደትዎ በፊት አስፈላጊ የሆኑ መመርያዎች

ሂደትዎ ቀጠሮ መቀየር ወይ መሰረዝ ካለበት ቀዶ ጥገና ባለሙያዎን ያሳውቁ። ከታመሙ ወይ ትኩሳት ካልዎት ለሂደቱ ቀጠሮ ከማስያዞ በፊት እባክዎትን ወደ ቀዶ ጥገና ባለሙያው ይደውሉ። ሂደቱ እስከሚካሄድበት ቀን አይጠብቁ።

**የሚከተሉት መመርያዊች ለደህንነቶ አስፈላጊዎች ናቸው። እባክዎትን መመርያዊቹን በጥንቃቄ ይከተሉ።**

ከታች እንደተቀመጠው ሂደትዎ ማደንዘኛ የሚያስፈልገው ከሆነ የፆም መመርያወውን ይከተሉ፡

| ደረቅ | ፈሳሽና አይስ ቺፕ | የጡት ወተት | የጨቅላ ህፃናት ፎርሙላ | የሰው ያልሆኑ ወተቶች |
|---|---|---|---|---|
| ከቀዶ ጥገናው በፊት ከ11 ፒኤም በኃላ ምግብ መመገብ አይቻልም። | እንዲመጡ ከተነገሮት 2 ሰዓት በፊት ‹‹ክሊር›› ፈሳሽ ወይ አይስ ቺፕ መውሰድ ይችላሉ።<br>ንጹህ ፈሳሽ ተብለው የሚጠቀሱት፣ የአፕል ጭማቂ፣ እንደ Gatorade የመሳሰሉ የስፖርት መጠጦችና ክሬም ወይ ወተት የሌለው ቡና ወይ ሻይ ያካትታል። ስኳር ወይ ማጣፈዓ መጨመር ይቻላል። | ሂደቱ ከሚካሄድበት 4 ሰዓት በፊት ጡት ማጥባት መቆም አለበት።<br>ሲርያል ወይ ማወፈርያ አይጨምሩ። | ሂደቱ ከሚካሄድበት 6 ሰዓት በፊት ጡት ማጥባት መቆም አለበት።<br>ሲርያል ወይ ማወፈርያ አይጨምሩ። | ሂደቱ ከሚካሄድበት 6 ሰዓት በፊት ጡት ማጥባት መቆም አለበት።<br>ሲርያል ወይ ማወፈርያ አይጨምሩ። |

- በቀዶ ጥገና ሀኪም ወይ ከሂደት በፊት አቅራቢው የተለየ መመርያ ካልተሰጦት እባክዎትን በገፅ 4 ላይ ያለውን የቆዳ ማፅዳት መመርያ ይተግብሩ።
- ቀዶ ጥገና ከማካሄዶ 24 ሰዓት በፊት አይላጩ ወይ ፀጉር መላጫ ምርቶችን አይጠቀሙ።
- ሎሽን፣ ሽቶ፣ የሚነፎ ምርቶች ሜክአፕ አይጠቀሙ።
- መታወቅያና መድሕን ካርድ፣ ክፍያ (በቼክ፣ ጥሬ ገንዘብ ወይ ክሬዲት ካርድ)፣ እንዲሁም የፋርማሲ ካርድ ይዘው ይምጡ።
- እባክዎት ውድ ንብረቶችና ጌጦችን እቤት አስቀምጠው ይምጡ። ሁሉንም ጌጦችና ቀለበት ያውጡ።
- እባክዎትን ኮንታክት ሌንሶን እቤት አስቀምጠው ይምጡ። መነፀር የሚያደርጉ ከሆነ መነፀር ማስቀመጫ ይዘው ይምጡ።
- ለጆሮ ማዳመጫ መሰርያ ማስቀመጫ የሚሆን ስምና የትውልድ ቀን ያለበትን ማስቀመጫ ያምጡ።
- ኦብስትራክቲቭ የመኝታ ኤፒን ካልዎት Inova ከሂደቱ በኋላ ተቀብሎ ለጊዝያዊ ጥቅም CPAP ክፍል ያቀርባል። ተመላልሰው እንዲታከሙ ቀጠሮ ከተያዘ የግል CPAP ወይ BiPAP ማሽን ማምጣት ይችላሉ።
- ሰፊና ምቹ የሆኑ ልብሶችን ይልበሱ።
- እቤትዎ የሚያደርስዎትን መጓጋዣ ያመቻቹ። ለደህንነቶ ሲባል ማድንዘዣ ከወሰዱ በኋላ ራስዎ እንዲያሽከረክሩ ወይ የህዝብ ማመላለሻ እንዲጠቀሙ **አይፈቀድሎትም**። ሓላፊነት የሚሰማው አዋቂ ከቤት ወደ ሆስፒታል ሊወስዶት ይገባል። የህዝብ ማመላለሻ ወይ መኪና መጋራት አገልግሎት የሚጠቀሙ ከሆነ ከሹፌሩ **ሌላ አዋቂ** ሊኖር ይገባል። ቀዶ ጥገና ካካሄዱ በመጀመርያዎቹ 24 ሰዓታት አዋቂ አብሮት እንዲኖር እናበረታታለን።
- አስቀደሞ የሚሰጥ መመርያ፣ ኑዛዜ ወይ የመወሰን ሀላፊነት ቅጂ ይዘው ይምጡ። አስቀድሚ የሚሰጥ መመርያ እንዲኖሮት እናበረታታለን። አስቀድሞ ስለሚሰጥ መመርያ ተጨማሪ ማወቅ ከፈለጉ **inova.org/advancedirective** ይጎብኙ።

ታካሚው ስለ ሕክምና ውሳኔ መስጠት ካልቻለ እባክዎትን ተገቢ የሆነ አዋቂ አብሯቸው እንዲመጣና የፍቃድ ቅፅ ላይ እንዲፈርም ያድርጉ።

ስም፡ ______________________________

ስልክ ቁጥር፡ ______________________________

# ከሂደት በፊት የቆዳ ማፅዳት መመርያዎች

ቀዶ ጥገና በተደረገበት ቦታ ያለውን የኢንፌክሽን ስጋት ለመቀነስ ቀዶ ጥገና ከማድረጎ በፊት እቤት ውስጥ ልዩ በሆነው ጀርም ገዳይ ማፅጃዎች ሰውነቶን ያፅዱ። ሰውነቶን በ4% ክሎረክስዲን ግሉኮንታ (እንዲሁም CHG በመባል ይታወቃል) በመጠቀም በተገቢ መልኩ ለማፅዳት እባክዎትን የሚከተለውን መመርያ ይከተሉ።

## CHG የት ይገኛል

CHG አንቲማይክሮባያል ለመግዛት መድሀኒት ማዘዣ አያስፈልጎትም። CHG በማንኛውም ፋርማሲ ይገኛል፤ ድጋፍ ለማግኘት ፋርማሲስቱን ወይ ቴክንሽኑን ይጠይቁ። አንዳንድ CHG ብራንድ ስሞች Hibiclens፣ Hibistat፣ Exidine እንዲሁም Hex-A-Clens ያካትታል።

በእያንዳንዱ ገላዎን በሚታጠቡበት ወቅት ከሁለት እስከ አራት ኦንስ ይጠቀሙ።

## CHG እቤት ውስጥ እንዴት መጠቀም ይቻላል

- ሰውነቶን ሲታጠቡ CHG ይጠቀሙ። መታጠብያ ገንዳ ውስጥ እንዳይገቡ።
- CHG ቀዶ ጥገና ከማድረጉ በፊት ምሽትና ቀዶ ጥገና በሚያደርጉበት ጥዋት ላይ ይጠቀሙ፤ ማለትም እቤት ውስጥ ሁለት የተለያየ ሻወር።
- **የመገጣጠምያ ወይ ስፓይን ቀዶ ጥገና እሚያደርጉ ከሆነ**፣ CHG ቀዶ ጥገና ከማድረጎ ሁለት ምሽትና ቀዶ ጥገና በሚደረግበት ጥዋት ላይ ባጠቃላይ ሶስት ጊዜ ይታጠቡ።

## CHG በመጠቀም እንዴት ቆዳችንን እናፀዳለን

1. መጀመርያ ምሽት ገላውን ይታጠቡ፣ ሲታጠቡ በማንኛውም ሳሙና ይታጠቡ።
2. CHG ከመጠቀም በፊት መደበኛውን ሳሙናና ሻምፖውን ከሰውነቶ እንዳፀዱ ያረጋግጡ።
3. የሻወሩን ውሃ ዘግተው በእጅዎ CHG ሰውነቶን ይቀቡ። እባክዎትን ፊቶን፣ ፀጉርና መራብያ አካሎትን እንዳይቀቡ።
4. ለሶስት ደቂቃ ያህል ቀዶ ጥገና የሚደረግበትን ክፍል ያፅዱ። ቀዶ ጥገና የሚደረግበትን የሰውነት ከክፍል የማይደርሱበት ከሆነ ሰውነቶን ሲታጠቡ ሰው እንዲያግዞት ያደርጉ። እባክዎትን እርስዎን ከመርዳታቸው በፊት እጃቸውን በሚገባ እንዲያፀዱ ያደርጓቸው።
5. CHG ተቀብተው ከጨረሱ በኋላና ሶስት ደቂቃ ከቆዩ በኋላ ውሃውን ደግመው በመክፈት CHG ከሰውነቶ ያፅዱ።
6. በንፁህ ደረቅ ፎጣ እራስዎትን በደንብ ያደርቁ።
7. ሎሽን፣ ፓውደር፣ ሽቶ ወይ ዴዶራንት እንዳይቀቡ።
8. ንፁህ ፒጃማ ወይ ልብስ ይልበሱ።
9. **የመገጣጠምያ ወይ ስፓይን ቀዶ ጥገና እሚያደርጉ ከሆነ**፣ ለሁለተኛ የምሽት ሻወር ሂደት ይድገሙ።
10. ቀዶ ጥገና በሚደረግበት ጥዋት ላይ ሰውነቶን ሲታጠቡ ከላይ የተጠቀሰውን መመርያ ይከተሉ፤ ነገር ግን ሳሙና ወይ ሻምፖ እንዳይጠቀሙ - CHG ብቻ ይጠቀሙ።

## CHG እና ፀጉር መላጨት

- CHG በቅርብ የተላጨ ሰውነት ላይ ከተቀባ ያቃጥላል። ቀዶ ጥገና ከማካሄዶ 24 ሰዓት በፊት አይላጩ ወይ ፀጉር መላጫ ምርቶችን አይጠቀሙ።
- ከ24 ሰዓት በፊት መላጨትን ከመረጡ እባክዎትን ቆዳዎን እንዳያቃጥሎት ወይ ፀጉር ወደ ሰውነትዎ እንዳይጣበቅ CHG ከመጠቀሞ በፊት ይላጩ።
- ለሂደቱ ፀጉር መላጨት አስፈላጊ ከሆነ በቀዶ ጥገና ክፍል ባሉት የቀዶ ጥገና ቡድን አባላት ይካሄዳል።

## CHG ጥንቃቄዎች

- CHG በመጠቀሞ ሰውነቶ ከቀላ ወይ ካሳከኮት ይህን መጠቀም በማቆም የቀዶ ጥገና ሀኪሞን ያግኙ።
- ለፊትዎ፣ ፀጉርና መራብያ ክፍል CHG አይጠቀሙ።
- ገላ ለመታጠብ CHG ብቻ ይጠቀሙ። መታጠብያ ገንዳ ውስጥ እንዳይገቡ። ገላዎን መታጠብ የማይችሉ ከሆነ ተጨማሪ መመርያ ለማግኘት ወደ ቀዶ ጥገና ፅህፈት ቤት ይደውሉ።

**ለህጻናት ታካሚዎች፡**

- እባክዎትን ትንሽ መጫወቻ ያምጡ (ለምሳሌ አሻንጉሊት፣ ብርድልብስ ወይ የጨርቅ አሻንጉሊት)።
- እባክዎትን ልብሶቹን ወደ ሆስፒታል ከማምጣቶ በፊት *ሁሉንም* ይጠብዋቸው።
- የህፃኑ ወላጅ ካልሆኑ እባክዎትን የአሳዳጊነት መረጃዎን ይዘው ይምጡ።
- የልጅዎን ሂደት ለማዘጋጀት ከልጆች ሂወት ቡድናችን ጋር ጉብኝት ቀጠሮ መያዝ ይቻላል። ጉብኝቱን ቀጠሮ ለመያዝ እባክዎት ወደ **706.858.6937** ይደውሉ።

ልጅዎ ልዩ የሰንሰሪ ፍላጎት ካለው እባክዎትን በቅድመ-ቀዶ ጥገና ቃለመጠየቅ ወቅት ለነርስዋ ያሳውቁ። ከልጅዎ ጋር በተሻለ መልኩ ለመግባባት እንዲያስችለን ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጅዎ ለመነጋገር የሚመርጠውን ዘዴ፣ ማነቃቅያ፣ የሚያስጨንቀው ነገርና የመግባባት ችግሮችን የሚያሳየውን ቅፅ ይሙሉ። በተጨማሪም ማሕበራዊ ታሪክ በ **inova.org/prepare** ማግኘት ይችላሉ።

ዕድምያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት *ሁሉም* የሂደት ምርመራዎችና ቀጠሮ የመያዝ ሂደት ላይ ወላጆቻቸው ወይ ሕጋዊ አሳዳጊያቸው መገኘት አለበት። ሂደቱ በሚካሄድበት ቀን የፍቃድ ቅፅ ላይ ለመፈረም ወላጆች መገኘት ያለባቸው ሲሆን ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ሆስፒታል ውስጥ መቆየት አለባቸው።

## ሂደቱ የሚኪያሄድበት ቀን

የሚመጡበት ሰዓት፡ ______________________________

ሂደት የሚካሄድበት ቀን፡ ______________________________

ሂደት የሚካሄድበት ሰዓት፡ ______________________________

## ሂደት የሚካሄድበት ቦታ፡

☐ Inova Loudoun Hospital

☐ Inova Loudoun Ambulatory Surgery Center

## ማገገምና ወደ ቤት መውጣት

- አማካኝ የማገገምያ ወቅት ሁለት እስከ አራት ሰዓት ነው ነገር ግን ቀዶ ጥገናውንና የጎንዮሽ ጉዳቱን መሰረት በማድረግ ከዚህ በላይ ሊሆን ይችላል።
- ከመውጣቶ በፊት እርስዎና አስታማሚዎ ከቀዶ ጥገና ባለሙያ መመርያና መድሀኒት ይታዘዝሎታል። እንዲሁም እቤት ውስጥ ለማገገም በሚገባ መዘጋጀቶን እናረጋግጣለን።

# የሂደት ክፍያዎን ሒሳብ መረዳት

- ሂደቱ ከመካሄዱ በፊት የ Inova ፋይናንስ አገልግሎት ክፍል የሚከተለውን ያደርጋል፡
  - ሽፋኖንና ጥቅሞችን ያረጋግጣል
  - ከመድህን ሽፋኖ አስፈላጊ የሆነውን ፈቃድ ያገኛል
  - የሚጠበቅቦትነ የፋይናንስ ሀላፊነት መረዳት ላይ ያግዘታል
  - የፋይናንስ ስምምነት ያዘጋጃል
- ልናገኝዎት ካልቻልን እባክዎትን በሂደቱ ላይ ለሚኖረው ማንኛውም የጋራ ክፍያ ወይ የጋራ መድህን ለመክፈል ዝግጁ ይሁኑ።
- ኮስመቲክ ሂደት ከተደረገ አስቀድሞ ክፍያ መከፈል አለበት።

## ከቀዶ ጥገና በኋላ የተለያዩ ክፍያ ደረሰኞችን እንደሚኖርዎት ይጠብቁ።

- ከቀዶ ጥገና ወይ ሂደት ጋር ለሚያያዙ ወጪዎች የቀዶ ጥገና አቅራቢው መጀመርያ ለመድህን አቅራቢዎ ያስከፍላል።
- እንደሚቀነስ ወጪ፣ የጋራ ክፍያ ወይ የጋራ መድህን የመሳሰሉ ተቀንሰው የቀረውን ሒሳብ ይሰጦታል።
- ከቀዶ ጥገና ቡድን አቅራቢዎች የተለያዩ ክፍያዎች ይደርሶታል። የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡

## የሆስፒታል ክፍያዎች፡

- ይህ ሂደቱ ወይ ቀዶ ጥገና ለተካሄደበት ሆስፒታል ወይ ቀዶ ጥገና ማእከል የሚከፈል ክፍያ ነው። ይህ ክፍያም ለሰራተኞች፣ አቅርቦቶችና ለቀረበው የቀዶ ጥገና አገልግሎት መሳርያ ወጪ የሚሸፍን ነው።
- ሒሳቡን የሚመለከቱ ጥያቄዎችና ክፍያዎች በሒሳብ ዝርዝሮ ላይ ወደ ተጠቀሰው ሆስፒታል/ተቋም መላክ አለበት። ወይ ወደ Inova የሒሳብ ፅሕፈት ቤት ማእከል በ**571.423.5750** ይደውሉ።
- ስለ የሚገመተው ሒሳብ ጥያቄ ካሎት እባክዎትን በ **703.858.8894** ወይ **703.858.8899** ይደውሉ። የቡድኑ አባላቶች ከሰኞ-ዓርብ ከ 8:30 ከሰዓት በፊት እስከ 4:30 ከሰዓት በኋላ ሊያግዞት ይችላል።

## የቀዶ ጥገና ሀኪም ክፍያ፡

- ይህን የተመለከቱ የክፍያ ጥያቄዎች ለተጠቀሰው ቀዶ ጥገና ባለሙያ መላክ አለበት።

## የማደንዘዣ ክፍያዎች፡

- ይህ በሂደቱ ግዜ በማደንዘዣ ባለሙያ ለሚሰጡት የማደንዘዣ ኣገልግሎት የሚውል ክፍያ ነው።
- ይህን ክፍያ የተመለከቱ ጥያቄዎች ካልዎት በሒሳብዎ ላይ ለተጠቀሰውን ማደንዘዣ ቡድን መላክ አለበት።

## አስፈላጊ ስልክ ቁጥሮች

| | |
|---|---|
| ዋና የሆስፒታል ኦፕሬተር | 703.858.6000 |
| Inova የቅድመ-ህክምና ግምገማ ክሊኒክ | 703.858.6768 |
| የፋይናንስ ማማከር | 703.858.8091 |
| Inova ማእከላዊ የክፍያ ፅሕፈት ቤት | 571.423.5750 |

# Inova Loudoun Hospital – ላንድዳውኒ ካምፓስ ካርታ




## መኪና ማቆምያ መረጃ

**Inova Loudoun Hospital**
44045 Riverside Pkwy., Leesburg, VA

ለታካሚዎችና ጠያቂዎች በ Inova Loudoun Hospital ካምፓስ መኪና ማቆምያ ይገኛል።

በ Inova Loudoun Hospital ለሂደት ቀጠሮ ያላቸው ታካሚዎች በደቡብ የሆስፒታሉን መግቢያ (44045) ምልክቶችን በመከተል በደቡብ የመኪና ማቆምያ ላይ ያቁሙ።

በ Inova Loudoun Ambulatory Surgery Center ለሂደት ቀጠሮ ያላቸው ታካሚዎች በ 44035 የሀኪሞች ፅህፈት ቤት ህንፃ አድርገው በመግባት በሰሜን በሚገኘው ጋራጅ ማቆም ይችላሉ።

በ Inova Loudoun Hospital ስላለው የመኪና ማቆምያ አገልግሎት አሁናዊ መረጃዎች ለማግኘት እባክዎትን **inova.org/visitloudoun** ይጎብኙ።

# ለሂደት መዘጋጀት

## Inova Loudoun Hospital

Inova Loudoun Hospital
44045 Riverside Pkwy.
Leesburg, VA 20176

G39277AM